


## ማስታወቂያ

- Leave Your Voice Message
- ደጀ ሰላም ማን ናት?
- To display Amharic Fonts

# February 10, 2011

### የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ አፅራረ ቤተ ክርስቲያንን ለመከላከል በሚያደረገው ጥረት ማንኛውንም ድጋፍ እንደሚሰጥ የአ/አበባ ሀ/ስብከት አስታወቀ

- **የፕሮቴስታንታዊ-ተሐድሶ-ኑፋቄ ጥመት - አሰግድ ሣህሉ እንደ ማሳያ (ከደብረ ይባቤ ቅዱስ ያሬድ ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ት/ቤት ዘገባ የተገኘ)**



ቀንደኛ የተሐድሶ ኑፋቄ አቀንቃኝ የተባለው አሰግድ ሣህለ

(ደጀ ሰላም፤ ፌብሩዋሪ 10/2011፤ የካቲት 3/2003 ዓ.ም)፦ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ሐዋርያዊ ተልእኮ ለማፋጠን እና ለማስፋፋት፣ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካት፣ ኮሌጁንም ከማንኛውም አጽራረ ቤተ ክርስቲያን አካላት ለመጠበቅ በሚያደርገው ጥረት ሁሉ ድጋፍ የሚሰጥ መሆኑን አስታወቀ። የሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት ይህን ያስታወቀው፣ የኮሌጁ አስተዳደር ጉባኤ የኮሌጁን የቅበላ መስፈርት ባለማሟላቱ ኅዳር 23 ቀን 2003 ዓ.ም ከትምህርት ገበታ ያገደው አሰግድ ሣህለ የተባለ ቀንደኛ የተሐድሶ ኑፋቄ አቀንቃኝ፣ *<<በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ውስጥ የቤተ ክርስቲያን አባል እንደሆነ የሚያቀርበው የመብት ጥያቄ ተቀባይነት የሌለውና በሀገረ ስብከታችን ውስጥ የቤተ ክርስቲያናችን አባል አለመሆኑን>>* በመግለጽ ለኮሌጁ በጻፈው ደብዳቤ ነው።

በቁጥር 1530/37/03 በቀን 26/05/03 ዓ.ም በሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ ንቡረ ዕድ አባ ገብረ ማርያም ገብረ ሥላሴ ተፈርሞ በአድራሻ ለቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ፣ በግልባጭ ለሀገረ ስብከቱ የስብከተ ወንጌል እና ትምህርት መምሪያ እና ለደብረ ይባቤ ቅዱስ ያሬድ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት የደረሰው ይኸው ደብዳቤ፣ አሰግድ *<<በቤተ ክርስቲያን ሕግ እና ደንብ መሠረት በሕጋዊ መንገድ በአባልነት ያልተደራጀ፣ በደብረ ይባቤ ቅዱስ ያሬድ ቤተ ክርስቲያን ሾልኮ በመግባት በአፍራሽ ተልእኮ ተሰማርቶ በመገኘቱ ከደብሩ የተገለለ>>* መሆኑን

አስታውሶ በሀገረ ስብከቱ ውስጥ በማንኛውም የአገልግሎት ዘርፍ እንዳልተመደበ ማረጋገጡን ግልጽ አድርጓል።

ጥር ሦስት ቀን 2003 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 501/05/04/03 የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ለአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ባቀረበው ጥያቄ መሠረት ዲያቆን አሰግድ ሣህሉን በተመለከተ በቢሮው የሚገኙትን መረጃዎች መላኩን ያመለክታል፤ ከዚያ በኋላም ከሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት እና ከደብረ ይባቤ ቅዱስ ያሬድ ቤተ ክርስቲያን የተገኙትን ዝርዝር ጉዳዮች ሲፈትሽ እንደ ቆየ ገልጧል።

ጽ/ቤቱ በዚህ ምርመራው የደረሰባቸውን መረጃዎች በስድስት ነጥቦች ለያይቶ አስረድቷል፤ **እነርሱም፡- 1ኛ)** ግለሰቡ የመኖሪያ ቦታው በደብረ ይባቤ ቅዱስ ያሬድ ቤተ ክርስቲያን አጥቢያ አለመሆኑ፤ **2ኛ)** በተለያዩ ጊዜያት ያለአጥቢያው በሰንበት ት/ቤት በአባልነት ሲንቀሳቀስ መቆየቱን፤ **3ኛ)** በነበረው ቆይታ ሁሉ ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ እና ከሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን ውጭ በሚያደርገው አፍራሽ እንቅስቃሴ የደብሩን ሰላም እና አገልግሎት ሲያውክ የቆየ መሆኑን፤ **4ኛ)** በዚህ ጥፋቱ በደብሩ አስተዳደር ርምጃ የተወሰደበት ቢሆንም የተለያዩ ክፍተቶችን በመጠቀም ያልተቋረጠ ሙከራ ሲያደርግ መቆየቱንና አሁንም በማድረግ ላይ መሆኑን፤ **5ኛ)** <<በሰበካ ጉባኤ አባልነት ተመዝግቤ የአባልነት ክፍያዬን ያለማቋረጥ በመክፈል አባል ለመሆኔ መረጃ ይሰጠኝ>> ብሎ ማመልከቻ አቅርቦ ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ መረጃ መውሰዱንና ይህም ስሕተት በመሆኑ ደብሩ ቀደም ሲል የተሰጠውን መረጃ በቁጥር 471/666/03 በተጻፈ ደብዳቤ መሻሩን፤ **6ኛ)** በደብሩ ይሁን

በሰንበት ት/ቤቱ ስም ስውር ተልእኮውን ለማስፈጸም እንዳይችል ሰንበት ት/ቤቱ በቁጥር ው/ያ/11/17/03 በተጻፈ ደብዳቤ የማያዳግም ውሳኔ ማስተላለፋንና ይህም ውሳኔ በሁሉም አካል ታውቆ ተግባራዊ እንዲደረግ መጠየቁን ያስረዳል፡፡

አሰግድ ሣህሉ ከኮሌጁ የቅበላ መስፈርቶች አንዱ የሆነውን በሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ወይም በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ የተፈረመበት የድጋፍ ደብዳቤ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ባለማቅረቡ እና በድጋፍ ደብዳቤ ስም ያቀረበውም ማስረጃ በሕገ ወጥ መንገድ ያገኘው በመሆኑ ኅዳር 23 ቀን 2003 ዓ.ም በኮሌጁ የአስተዳደር ጉባኤ መታገዱን መዘገባችንይታወሳል (የዲሴምበር 4/2010፤ ኅዳር 25/2003 ዓ.ም ይመልከቱ)፡፡

ከእገዳው በኋላ አሰግድ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መናገሻ ምድብ ችሎት <<አላግባብ ከትምህርት ገበታው እንደታገደ>> አድርጎ በኮሌጁ ላይ ክስ መመሥረቱ ታውቋል፡፡ ፍርድ ቤቱ *<<ጉዳዩ ውሳኔ እስኪሰጥበት ድረስ ግለሰቡ ትምህርቱን እየተከታተለ እንዲቆይ ትእዛዝ አስተላልፏል>>* ቢባልም ኮሌጁ የወከላቸው ጠበቃ አቶ ደስታ በርሄ ጥር 27 ቀን 2003 ዓ.ም ለችሎቱ ባሰሙት ምላሽ የአሰግድ ችግር በዋናነት ሃይማኖታዊ መሆኑንና ሃይማኖታዊ ሕጸጽ እንዳለበት ኮሌጁ ከደብረ ይባቤ ቅዱስ ያሬድ ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ት/ቤት እና ከአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ባገኘው ማስረጃ ያረጋገጠ መሆኑን፣ በኮሌጁ በማታው ክፍለ ጊዜ ተመዝግቦ ትምህርቱን በዲግሪው መርሐ ግብር ለመቀጠል ሲጠይቅ በቅበላ መስፈርቱ መሠረት በቂ ማስረጃ አለማቅረቡን፣ ባለበት የሃይማኖት ሕጸጽ ሳቢያ በዲፕሎማው

መርሐ ግብር ትምህርቱን በ 1995 ዓ.ም ባጠናቀቀበት ወቅት ዲፕሎማው ሳይሰጠው መቆየቱን ማስረዳታቸው ተዘግቧል።

አሰግድ በተጠቀሱት ምክንያቶች ከኮሌጁ እንዲባረር መወሰኑን ያስረዱት ጠበቃው፣ የግለሰቡ ችግር በዋናነት ሃይማኖታዊ ከሆነ ዘንድ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 11 ንኡስ አንቀጽ 1 እና 3 መንግሥት እና ሃይማኖት የተለያዩ መሆናቸውን፣ መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ እንደማይገባ ሃይማኖትም በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ እንደማይገባ መደንገጉን፤ ኮሌጁ በቅዱስ ሲኖዶስ ተፈቅዶ በተሰጠው ሕግ መሠረት የሚያስተምራቸውን ደቀ መዛሙርት የሚመርጥበት መስፈርት ያለውና ከዚህም ጋራ በተያያዘ የተማሪዎች መተዳደሪያ ደንብ ያወጣ መሆኑን ጠቅሰው ጉዳዩ በዚሁ የተቋሙ አሠራር ብቻ ሊታይ የሚችል በመሆኑ ምስክር፣ ድርድር ሳያስፈልግ ፍርድ ቤቱ እንዲያሰናብታቸው መጠየቃቸው ተመልክቷል። ይሁንና ፍርድ ቤቱ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ለመስጠት ለመጋቢት 27 ቀን 2003 ዓ.ም መቅጠሩ ታውቋል።

## የፕሮቴስታንታዊ-ተሐድሶ-ኑፋቄ ጥውየት - አሰግድ ሣህሉ እንደ ማሳያ

አሰግድ ሣህሉ በደብረ ይባቤ ቅዱስ ያሬድ ቤተ ክርስቲያን የዉሉደ ያሬድ ሰንበት ት/ቤት የተሐድሶ ኑፋቄን ለማስፋፋት፣ አንዳንድ የሰንበት ት/ቤቱን ወጣቶች ከእናት ቤተ ክርስቲያን ወደ <<ሙሉ ወንጌል>> አዳራሽ ለመውሰድ ሲያደርግ የቆየውን እንቅስቃሴ አስመልክቶ በጥብቅ ሲከታተል በቆየው የሰንበት ት/ቤቱ ሥራ አመራር ኮሚቴ የተዘጋጀው ባለ 40 ገጽ ሰነድ ያስረዳል። እንደ ዘገባው ማብራሪያ አሰግድ ሣህሉ ከሚኖርበት ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 11/12 የቤት ቁጥር 417

በተለምዶ *ቡልጋሪያ* ተብሎ ከሚጠራው የደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል - *የከርቸሌው ሚካኤል* አካባቢ ያለሰበካው ወደ ደብረ ይባቤ ቅዱስ ያሬድ ቤተ ክርስቲያን መጥቶ በዉሉደ ያሬድ ሰንበት ት/ቤት በ1985 ዓ.ም የተመዘገበው ሰንበት ት/ቤቱ በወቅቱ ያጋጠመውን የአገልግሎት መዳከም ተመልክቶ ስውር የተሐድሶ ኑፋቄ ተልእኮውን ለማራመድ እንዲያመቸው ነው።

በሂደት የሰንበት ት/ቤቱ <<የትምህርተ ሃይማኖት አስተማሪ>>፣ የሥራ አመራር አባል እና የትምህርት ክፍል ሰብሳቢ እስከመሆን የደረሰው አሰግድ ወጣቶችን ከቤተ ክርስቲያን ጉያ በማውጣት የሚታወቁትን ግርማ በቀለ(ይህ ግለሰብ ከሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤት በኑፋቄው በአባቶች ተወግዞ ከተባረረ በኋላ **<<የእውነት ቃል አገልግሎት>>** የተባለ የተሐድሶ ኑፋቄ አራማጅ ድርጅት የመሠረተ ነው)፣ <<አባ>> ዮናስ(በ1990 ዓ.ም. ሚያዝያ 28 ቀን ራሳቸውን ገልጠው የፕሮቴስታንታዊ ተሐድሶ ኑፋቄያቸውን በአደባባይ በማስመስከራቸው ከቤተ ክህነት አዳራሽ ተወግዘው ከተለዩት አንዱ)፣ እነ ስዩም ያሚን ወደ ሰንበት ት/ቤቱ እየጋበዘ እንዲያስተምሩ አድርጓል።

በ1986 ዓ.ም ነሐሴ ወር በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ አዘጋጅነት በጠቅላይ ቤተ ክህነት የስብከተ ወንጌል አዳራሽ በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት እና በሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን በተሰጠው የአንድ ወር ኮርስ ላይ ሰንበት ት/ቤቱን ወክሎ የተሳተፈው አሰግድ፣ **<<ኢየሱስ ክርስቶስ አሁንም በአብ ቀኝ ቆሞ ያማልዳል፤>>** በማለት በይፋ ይከራከር እንደነበርና በኮርሰኞቹ ምላሽ ይሰጠው እንደነበር ሰነዱ

ያስታውሳል። ከዚህ በኋላ አሰግድን ጨምሮ በ1984 ዓ.ም <<የተዳከመውን የቅዱስ ያሬድ ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ት/ቤትን እናጠናክራለን>> በሚል ሽፋን የአጥቢያ ሰንበት ት/ቤታቸውን ትተው ከመጡ ሌሎች ሁለት ግለሰቦች(በሚያስደንቅ አኳኋን አሁን የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ሆነዋል) ጋራ እንዲታገዱ የሰንበት ት/ቤቱ ወጣቶች የደብሩን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ አስተዳደር ይጠይቃሉ።

በየጊዜው ይደረግ የነበረው የደብሩ አስተዳዳሪዎች መለዋወጥ ጥያቄው በወቅቱ ሰሚ አግኝቶ ርምጃ እንዳይወሰድ ዕንቅፋት ፈጥሮ እንደነበር የሚያመለክተው ሰነዱ፣ ጥቆማው ከቀረበላቸው የወቅቱ የደብሩ አስተዳዳሪዎች አንዱ የትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት ዋና አስኪያጅ ሊቀ ካህናት ብርሃኑ ገብረ ዐማኑኤል ሁኔታውን በመረዳት አሰግድን ጠርተው፣ <<መማር ከፈለግህ እኔ ጋራ ቢሮዬ እየመጣህ አስተምርሃለሁ፤ ለጊዜው ግን ወደ ሰንበት ት/ቤት አትሂድ>> ብለው እንደመከሩት ገልጧል። በቢሯቸው ጠርተው ባነጋገሩበት ጊዜም ግለሰቡ የኑፋቄ ችግር እንዳለበት ቢረዱም ለሦስት ወራት ደብሩን አስተዳድረው በመቀየራቸው ርምጃ ሳይወሰድ መቅረቱን ዘግቧል።

በዚህ ሁሉ መካከል ግን አሰግድ የተሐድሶ ኑፋቄ እንቅስቃሴ ይራመድባቸው በነበሩ የቤት ለቤት ጽዋ ማኅበራት እና በየአዳራሹ በሚካሄዱ ጉባኤያት እንደሚሳተፍ፣ ሰንበት ተማሪዎችንም እያግባባ እንደሚወስድ፣ <<የክርስቶስ ሥጋ እና ደም ተቀበልንም አልተቀበልንም ለውጥ የለውም>> እያለ እንደሚቀስጥ፣ የካህናት አባቶችን ክብር እና ማዕርግ ንቆ ሲያበቃ ሌሎችም እንዲንቁት እንደሚቀሰቅስ

መረጃው በመድረሱ የሰንበት ት/ቤቱ አመራር ይኸው በዐይን ምስክሮች ተገልጦ በጉባኤ እንዲመሰከርበት በማድረግ ያጋልጠዋል። ይህም በደብሩ አስተዳዳሪ አማካይነት ለሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤው ቀርቦ ከታየ በኋላ ጥቅምት 10 ቀን 1988 ዓ.ም ከሰበካ ጉባኤው ጽ/ቤት በተጻፈ ደብዳቤ አሰግድ ከሰንበት ት/ቤቱ ሊታገድ ችሏል።

አሰግድ ግን <<ያለአግባብ ከሰንበት ት/ቤቱ ታግጃለሁ፤ ዳኝነት ይታይልኝ>> ብሎ ለአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት ያመለክታል። ሀገረ ስብከቱ ጉዳዩን እንዲያጣሩ የላካቸው ሁለት ልኡካንም መጋቢት 23 ቀን 1988 ዓ.ም የደብሩ የስብከተ ወንጌል ኮሚቴ የወከላቸው አራት አባላት ባሉበት በአሰግድ ላይ ማስረጃ ባቀረቡት የሰንበት ት/ቤቱ ተወካዮች ጠያቂነት አሰግድ እየመለሰ በሰንበት ት/ቤቱ አዳራሽ በጥያቄ እና መልስ የታገዘ ውይይት ይደረጋል። በውይይቱ ላይ የሀገረ ስብከቱ ተወካዮች አሰግድን፣ <<በአንደበትህ ከተናገርከው ቃል በቂ ማስረጃ ይዘንብሃል፤ ስለምን ጥፋትህን አታምንም□>> ይሉታል። በወቅቱ የደብሩ አስተዳዳሪ የነበሩት ቆሞስ አባ ሀብተ ሚካኤል ታደሰም፣ <<አሰግድ ጥፋትህን እመንና ቀኖና እንሰጥሃለን፤ እባክህ ብትመለስ ይሻልሃል፤>> በማለት ይማፀኑታል። ልቡን እንደ እብነ አድማስ ያደነደነው አሰግድም የስብሰባው ቃለ ጉባኤ እና የደብሩ አስተዳደር የውሳኔ መነሻ ወደ ሀገረ ስብከቱ ሳይላክ፣ *<<እኔ ተሐድሶ አይደለሁም፤ እኔ ራሴን የማውቀው የቤተ ክርስቲያን ዶግማ እና ቀኖና ጠንቅቄ መኖሬን ነው፤ ነገር ግን እናንተ የለም ተሐድሶ ነህ ካላችሁኝ ክፉ እና ደጉን ከለየሁበትና ከአደግሁበት ሰንበት*

*ት/ቤት መለየት አልፈልግምና ቀኖና ተሰጥቶኝ እንድመለስ በልዑል እግዚአብሔር ስም አመለክታለሁ፤>>* ብሎ ለደብሩ ደብዳቤ ይጽፋል።

የደብሩ አስተዳደር በዕለቱ የተደረገውን ውይይት እና የደብሩን አስተያየት በማካተት ለሀገረ ስብከቱ ይልካል። ሀገረ ስብከቱም ልኡካኑ ያቀረቡትን ሪፓርት፣ የደብሩን አስተያየት እና አሰግድ ለደብሩ የጻፈውን ደብዳቤ በማገናዘብ፣ <<ከቀኖና አንጻ አመክሮ ስለሆነ ወደ ሰንበት ት/ቤቱ ከመመለሱ በፊት እንደማንኛውም አማኝ ለተወሰነ ጊዜ በስብከተ ወንጌል ትምህርት እየተማረ እንዲቆይ>> የሚል ውሳኔ በቁጥር 2/58/37/88 ቀን 11/11/88 ዓ.ም በወቅቱ *ሥራ* አስኪያጅ በነበሩት መልአከ ሰላም ቆሞስ አባ ገብረ ሚካኤል በየነ(አሁን ብፁዕ አቡነ እስጢፋኖስ) *ፊ*ርማ ያስተላልፋል። ይህን ውሳኔ የደብሩ አስተዳደር በቁጥር 63/534/88 በቀን 29/11/88 ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤ ለአሰግድ ያሳውቀዋል። የውሳኔውን ተገቢነት አስመልክቶ በዘገባው ላይ የሚከተለው አስተያየት ሰፍሯል፡- *<<እዚህ ላይ በጣም የሚያሳዝነው በቤተ ክርስቲያን ላይ ኑፋቄ ለሚዘራ፣ ወጣቶችን ከእናት ቤተ ክርስቲያን ለሚያስኮበልል፣ ቅዱሳንን እና የቤተ ክርስቲያን አባቶችን ለሚንቅ፣ ቅዱስ ቁርባን አያድንም ብሎ ለሚያስተምር ሰው የንስሐ አባቱ ቀኖና እንዲሰጡት እና የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት እግር ሥር ተቀምጦ እንዲማር አባቶች እንዲመደቡለት አለመደረጉ ነው፤ የተሰጠው ቀኖና እና አመክሮ ለአንድ ወር ብቻ በማታው የስብከተ ወንጌል መርሐ ግብር እየተገኘ እንዲማር ነው።>>*

ሆኖም አሰግድ ይህ ደብዳቤ ከደረሰው ቀን ጀምሮ በማታው የስብከተ ወንጌል መርሐ ግብር ይሁን በዕለተ ሰንበት ቅዳሴ ለአንድም ጊዜ ስንኳ ተምሮም አስቀድሶም እንደማያውቅ በሰንበት ት/ቤቱ የተመደቡት የክትትል ቡድን አባላት ማረጋገጣቸውን ዘገባው ያስረዳል። የተባለው አንድ ወር ሲደርስ ግን ከቀኗ አንዲት ሳያሳልፍ(በ 29/12/88 ዓ.ም) ለደብሩ ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት <<በሥራ ምክንያት አልፎ አልፎ በስብከተ ወንጌል መርሐ ግብር ላይ ባልገኝም በአብዛኛው ጊዜ ግን ተገኝቼ ተምሬያለሁና የተሰጠኝ የጊዜ ገደብ ስለተጠናቀቀ ወደ ሰንበት ት/ቤት ለመግባት ሙሉ ፈቃዳችሁን እንድትገልጹልኝ እጠይቃለሁ>> የሚል ደብዳቤ ያስገባል፤ ይህንኑም ለሰንበት ት/ቤቱ አባላት ያስወራል።

እውነቱ ግን አሰግድ ቀኖናውን ተቀብዬ እንደታዘዝሁት ፈጽሜያለሁ ባለ ማግሥት ከጳጉሜ 1 - 5 ቀን 1988 ዓ.ም ለአምስት ተከታታይ ቀናት አሁን በፈረሰው የጎተራ ማሳለጫ ፊት ለፊት በሚገኘው የጎተራ <<ሙሉ ወንጌል>> አማኞች የጸሎት ቤት በተካሄደው ጉባኤ ላይ ከመሰሎቹ ጋራ ተካፍሎ ሲወጣ መረጋገጡ ነው። ይህን መነሻ በማድረግ 55 የሰንበት ት/ቤቱ አባላት አሰግድ የለየለት መናፍቅ በመሆኑ ከሰንበት ት/ቤቱ እንዲታገድ እንጂ ወደ ሰንበት ት/ቤቱ እንዳይመለስ የሚጠይቀውን አቤቱታቸውን በፊርማቸው በማረጋገጥ ለሰንበት ት/ቤቱ ሥራ አመራር ኮሚቴ ያቀርባሉ። ኮሚቴውም ይህንኑ ካጣራ በኋላ ሐሳቡን በማጽናት ለደብሩ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ያስታውቃል።

በዚህ ውሳኔ ኀይል ከአንድ ዓመት በላይ ወደ ደብሩ ሳይገባ ዙሪያውን ሲያንዣብብ የቆየው አሰግድ የደብሩ አስተዳዳሪ፣ የሰበካ ጉባኤ አባላት እና የደብሩ ዋና ጸሐፊ መቀየራቸውን ሲያረጋግጥ በተለይ አዲስ የተመደበው የሰበካ ጉባኤ ጸሐፊ እንደሚረዳው ሲተማመን ለአዲሱ የደብሩ አስተዳዳሪ <<ወደ ሰንበት ት/ቤቱ ልመለስ>> ሲል ጥያቄውን አቀረበ፤ የደብሩ ዋና ጸሐፊም የደብሩን አስተዳዳሪ ስላሳመነለት <<አሰግድ ቀኖናውን ስለጨረሰ ወደ ሰንበት ት/ቤት ይመለስ>> የሚል ደብዳቤ ተጻፈለት። ይህን ውሳኔ የሰማው የሰንበት ት/ቤቱ አመራርም <<በእውነት ከልቡ አምኖበት፣ እስከ ዛሬ የመናፍቃንን ስውር ዓላማ ማራመዱ ጸጽቶት ቀኖናውን ከፈጸመ ወደ ሰንበት ት/ቤቱ ከመመለሱ በፊት በስብከተ ወንጌል መርሐ ግብር እና ከዕለተ ሰንበት ቅዳሴ በኋላ እስከ ዛሬ ሲያካሂድ የነበረውን የመናፍቃን ድብቅ ሤራ በይፋ እንዲገልጥ>> የሚጠይቅ ደብዳቤ ለደብሩ ጽ/ቤት ይልካል።

በወቅቱ የደብሩ አስተዳዳሪ የነበሩት መልአከ ይባቤ ተስፋ ሚካኤል መርሻ በአንድ የሰንበት ቅዳሴ ቀን አሰግድን አጠገባቸው አቁመው፣ <<**ምእመናን፣ ይህ የምትመለከቱት ልጅ አስቀድሞ የተሐድሶ አራማጅ ነበር፤ አሁን ግን ጥፋቱን አምኖ ቀኖናውን ተቀብሏል፤ ምእመናን እልል በሉ፤**>> ሲሉ ተናገሩ። አሰግድም ጥፋቱን አምኖ ቀኖናውን ፈጽሞ መመለሱን እንዲናገር ዕድል ሲሰጠው፣ **<<ምእመናን፡- እኔ ተሐድሶ አይደለሁም፤ እኔ የቤተ ክርስቲያን ዶግማ እና ቀኖና ጠንቅቄ የምኖር ነኝ፤ ነገር ግን አንዳንዶች ስሜን ሲያጠፉ ነው፤**>> ብሎ የአዞ እምባውን ለቀቀው፤ ምእመናንም የደብሩ አስተዳዳሪ በተናገሩት እና አሰግድ በሰጠው የአባይ ምስክርነት ግራ ቢጋቡም በማልቀሱ ግን አዘኑለት። የሰንበት ት/ቤቱ

**ሥራ አመራር አባላት ግን <<የፈለገው ነገር ቢመጣ እኛን ያስወጡን እንጂ እርሱ ወደ ሰንበት ት/ቤት አይገባም>>** ብለው በአቋማቸው ጸኑ።

ሁኔታውን አስመልክቶ የዘገባው አጠናቃሪ፣ <<የአሰግድ ዋና ዓላማ **ለምእመናን የተሐድሶ ኑፋቄ አራማጅ አለመሆኑን ተናግሮ ስሙን ለማደስ** እንዲሁም ለእርሱ እጅግ በጣም ጠቃሚ የሆነውን በደብሩ አስተዳዳሪ የተጻፈለትን **ቀኖናውን ስለጨረሰ ወደ ሰንበት ት/ቤት ይመለስ** የሚለውን ደብዳቤ መያዝ እንጂ ወደ ሰንበት ት/ቤቱ መመለስ አልነበረም፤>> ብለዋል። ዘጋቢው እንዳሉትም ውስጠ ተኩላው አሰግድ የልቡን ከፈጸመ በኋላ እስከ 1996 ዓ.ም ድረስ ለአምስት ዓመታት ወደ ቅዱስ ያሬድ ቤተ ክርስቲያን ደርሶ እንደማያውቅ ተገልጧል። ይሁንና ከዚያ በኋላ በተመሳሳይ የኑፋቄ ተግባሩ ከጃቴ ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያንም እንደተባረረ የደብሩ አስተዳዳሪ የነበሩት ቆሞስ አባ ክፍለ ዮሐንስ ለመልአከ ይባቤ ተስፋ ሚካኤል መርሻ የነገሯቸውን ምስክርነት ዘገባው አስፍሯል። በዚህም መልአከ ይባቤ ተስፋ ሚካኤል ቀደም ሲል አሰግድ ቀኖናውን ፈጽሞ ወደ ሰንበት ት/ቤቱ እንደተመለሰ በቀናነት ለሰንበት ት/ቤቱ የጻፉትን ደብዳቤ ለመሻር ወስነው የሰንበት ት/ቤቱን ጥያቄ ሲጠባበቁ ከአስተዳዳሪነታቸው መነሣታቸውን ዘገባው በቁጭት ያስታውሳል።

ከዚህ በኋላ ወደ ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ በማታው ክፍለ ጊዜ ገብቶ በዲፕሎማ መርሐ ግብር መማር የጀመረው አሰግድ በክፍል ውስጥ በጥራዝ ነጠቅ የኑፋቄ ሐሳቦች መምህራኑን እና ደቀ መዛሙርቱን መነትረክ በመጀመሩ የግለሰቡን ዓላማ እና ተልእኮ የሚያጠና ሦስት ደቀ መዛሙርት የሚገኙበት ኮሚቴ ይቋቋማል።

ይህን ተከትሎ አሰግድ ትምህርቱን <<ሲያጠናቅቅ>> በኮሌጁ ዲፕሎማው ሳይሰጠው ተይዞበት ይቆያል። ዘገባው እንደሚለው፣ እንዴት እንደተፈጸመ በማይታወቅ አኳኋን አሰግድ የተያዘበትን ዲፕሎማ ከኮሌጁ ቆይቶ ተቀብሏል።

በ 2003 ዓ.ም በዲግሪው መርሐ ግብር ትምህርቱን በማታው ክፍለ ጊዜ ለመቀጠል ለኮሌጁ ያመለከተው አሰግድ፣ ከነበረበት ደብር የአስተዳዳሪው ወይም የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ፊርማ እና ማኅተም ያረፈበት፣ በአገልግሎት ላይ ስለመሆኑና ተመርቆ ሲወጣ ቤተ ክርስቲያኒቱን ተመልሶ እንደሚያገለግል ዋስትና የሚሰጥ ደብዳቤ እንዲያቀርብ ይጠየቃል። ይሁንና የደብረ ይባቤ ቅዱስ ያሬድ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ማንነቱን በውል የሚያውቅ በመሆኑ የትብብር ደብዳቤውን ስለማይጽፍለት፣ ቀሲስ አስቻለው መሐሪ የተባሉ ግብር አበሩን በመላክ **የደብሩ ሰበካ ጉባኤ አባል መሆኑን** የሚገልጽ ደብዳቤ ለቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ እንዲጻፍለት ኅዳር አንድ ቀን 2003 ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤ ይጠይቃል።

ደብዳቤውን የተመለከተው የወቅቱ የደብሩ ዋና ጸሐፊ ዲያቆን ክብረ በዓል ዐሥራትም ከደብሩ አስተዳዳሪ እና ከሰንበት ት/ቤቱ አመራር ጋራ አሰግድን በተመለከተ በቂ መረጃ ጠይቆ ለማግኘት ቢችልም ይህን ጥረት ሳያደርግ ራሱን ከተጠያቂነት ነጻ ለማድረግ ብቻ፣ አሰግድ የአራት ዓመት(ከ 2000 - 2003 ዓ.ም) የሰበካ ጉባኤ ውዝፍ(ብር 96) እንዲከፍል በማድረግ በ 01/03/2003 ዓ.ም ያስገባውን የትብብር መጠየቂያ ደብዳቤ ዕለቱኑ <<የንስሐ አባቱ ነኝ>> ላሉት ቀሲስ ተጠምቀ አስፍሓ አስተያየት እንዲሰጡበት ይመራላቸዋል። የንስሐ አባቱም

**<<በእኔ ንስሐ አባትነት የተመዘገበ እና የሰበካ ጉባኤ ክፍያውንም ወቅቱን ጠብቆ እየከፈለ መሆኑን አረጋግጣለሁ>>** በማለት በውክልና በተላከላቸው ደብዳቤ ላይ ይፈርማሉ። ዘገባው አሰግድ በርቀት(በውክልና በመላላክ) የንስሐ አባቱን እና የደብሩን ዋና ጸሐፊ በማግባባት ዓላማውን ለማሳካት የሞከረበትን መንገድ ሲያስረዳ፣ <<ከአፀራረ ቤተ ክርስቲያን በሚጎርፍለት የገንዘብ ድጋፍ በመደለል>> ሊሆን እንደሚችል የደጀ ሰላምን ዜና በመጥቀስ ያስረዳል።

በመጨረሻም በደብሩ ዋና ጸሐፊ በዲያቆን ክብረ በዓል ዐሥራት ፊርማ አሰግድ በደብረ ይባቤ ቅዱስ ያሬድ ቤተ ክርስቲያን <<የንስሐ አባት ይዞ፣ ተገቢውን የአባልነት ክፍያ አሟልቶ የሚገኝ መሆኑን>> በመግለጽ ለቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ በቁጥር 200/88/03 በቀን 06/03/03 የትብብር ደብዳቤ ተጽፎ በቀሲስ አስቻለው መሐሪ በኩል ተላከለት። ይህ በቅሰጣ የተገኘ የተልእኮ ደብዳቤ ግን በኮሌጁ የበላይ ሐላፊ ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ ዘንድ ተቀባይነት አላገኘም።

ስለሆነም አሰግድ ዐይኑን በጨው አጥቦ ራሱ ደብሩ ድረስ በመሄድ አስተዳዳሪውን መልአከ ገነት በቀለ ዘውዴን የትብብር ደብዳቤ እንዲጽፉለት ይጠይቃቸዋል። እርሳቸውም ዋና ጸሐፊው ያለእርሳቸው ዕውቅና በራሱ ፊርማ የጻፈለትን ደብዳቤ ሲመልስ የጠየቀውን ደብዳቤ እንደሚጽፉለት በብልኀት ይነግሩታል። ብልጡ አሰግድም የደብዳቤውን ኦሪጅናሌ ሳይሆን ቅጅውን ያቀርባል። ብልጥ አላንድ ቀን አይበልጥምና አስተዳዳሪው መልአከ ገነት በቀለ ዘውዴም **<<ዋናውን የማታመጣ ከሆነ ከዛሬ ጀምሮ እንዳትመጣ>>** ብለው አሳፍረው ሸኝተውታል። በቁጥር

417/666/03 በቀን 17/05/03 ዓ.ም ለቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ በጻፉት ደብዳቤም <<የአሰግድ ንስሐ አባት ነኝ>> ያሉት ካህን አስተያየታቸውን በመግለጽ በአድራሻ ቁጥር 200/88/03 በቀን 06/03/2003 ዓ.ም ለኮሌጁ ያስተላለፉት መልእክት መሻሩን አሳውቀዋል፡፡

አሰግድ ቀደም ሲል ወደ ምሥራቀ ፀሐይ ቀበና መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ሄዶ የነበረ ቢሆንም የአጥቢያው አባልም አገልጋይም ባለመሆኑ የትብብር ደብዳቤ ሊጻፍለት እንደማይችል በአስተዳዳሪው ተነግሮት መመለሱን መዘገባችን ይታወሳል - **የኦርቶዶክሳውያኑ አባቶች እና ወጣቶች ቀናዒነት እና መተባበር ምሳሌነት ያለው ሲሆን የተሐድሶ ኑፋቄ አቀንቃኙ አሰግድ ሣህሉ ጥውየት(ክፋት እና ጥመት) እንዲሁም ኀፍረተ ቢስነት ደግሞ እግዚኦ የሚያሰኝ ነው!!**

<u>ማስታወሻ</u>፡- **አሰግድ በኮሌጁ ላይ ላቀረበው ክስ እና የኮሌጁ ጠበቃ በሰጡት ምላሽ ላይ በፍርድ ቤት የሚሰጠው ውሳኔ እስከ መጋቢት 27 ቀን 2003 ዓ.ም ቢዘገይም የአሰግድን ሃይማኖታዊ ሕጸጽ ተመልክቶ የመወሰን ክህነታዊ ሥልጣኑ እና አስተዳደራዊ ችሎታው ያላት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን መሆኗን እናምናለን፡፡ የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ደግሞ የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት በደብዳቤው ላይ እንዳመለከተው የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ሐዋርያዊ ተልእኮ ለማፋጠን እና ለማስፋፋት የተቋቋመ እንጂ የተሐድሶ ኑፋቄ አዝማቾች የቤተ ክርስቲያኒቱን ሀብት እየተጣቡ የሚደራጁበት መደብር አይደለም፡፡ ከዚህ አኳያ ሀገረ ስብከቱ እና መንፈሳዊ ኮሌጁ በአሠራር ቅንጅት እና በመረጃ**

ልውውጥ ያሳዩት ተቋማዊ መገናዘብ በቤተ ክርስቲያን ህልውና ላይ ግልጽ እና ቅርብ አደጋ የጋረጠውን የፕሮቴስታንታዊ ተሐድሶ መዋቅራዊ እንቅስቃሴ ከመሠረቱ ለማፍለስ እየተደረገ ላለው ጥረት መንፈሳዊ ብርታት የሚሰጥ ነው፡፡

የደብረ ይባቤ ቅዱስ ያሬድ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ እና የዉሉደ ያሬድ ሰንብት ት/ቤት አመራርም ከመለው አባሎቻችሁ ጋራ፣ አመቺ ጊዜ እየጠበቀ ስውር ተልእኮውን ለማስፈጸም ያልተቋረጠ ሙከራ ያደረገውን የኑፋቄ አቀንቃኝ በጥብዐተ ኅሊና በቀጣይነት በማጋለጥ በፈጸማችሁት አብነታዊ ተጋድሎ ኦርቶዶክሳዊ ግዴታችሁን በመወጣታችሁ ያለንን የላቀ አክብሮት እንገልጽላችኋለን፡፡ ዘገባችሁ ለታሪክ የሚቀመጥ ብቻ ሳይሆን በአንድ በኩል የፕሮቴስታንታዊ-ተሐድሶ-ኑፋቄ አቀንቃኞች የቤተ ክርስቲያኒቱን አስተዳደራዊ መዋቅር የዓላማቸው ጥገኛ ለማድረግ ምን ያህል እንደሚማስኑ በሌላ በኩል ኦርቶዶክሳውያን ሳይተኙ ተግተው ሳያንቀላፉ ነቅተው ሊያተኩሩበት ስለሚገባው ቁምነገር(ክፍተት) ጥቁምታ የመስጠት ፋይዳ እንዳለው ተስፋ አለን፡፡ ሰልፋቸውን እንደ እናንተ፣ ከእናንተ ጋራ ለሚያደርጉት ሁሉ ተጋድሏቸው እንዲሰምር በዚህ አጋጣሚ ያለንን አጋርነት ልንገልጽላቸው እንወዳለን፡፡

Email This BlogThis! Share to Twitter Share to Facebook Share to Google Buzz

**26 አስተያየቶች:**

wossene said...

ደጀሰላሞች እንዴት ከረማችሁ ያወጣችሁት መረጃ በጣም ጠቃሚ በመሆኑ አመሠግናለሁ እንዲህእንዳሁኑ ያባቶች ትብብር ከቀጠለና አሰራሩን ካፋጠኑት ቤተክርስቲናችንንና ምእመናንን መጠበቅ እንችላለን
ደጀሰላሞች እባካችሁን በነካካ እጃችሁ ወደ ጀርመን በተለይም(ቪስባደን ቅዱስጊዮርጊስ)
ላይ ያለውን የተሀድሶ ምእመናንን የመንጠቅ ሴራ አጋልጡልን ቄስ ሆኖ የሚቀስጠው ግለሰብ
መናፍቅ የነበረና የምንፍቅና መጻሐፍ የጻፈና ጭራ መጽሔትን አሁንም የሚያፋፍል ደፋር ነው እባካችሁን
ድረሱልን"የቅዱሳን አምለክ ቤተክርስቲያንን ይጠብቅልን

February 10, 2011

Anonymous said...

kinibiru arif new!!! ketilubet
ቅንብሩ አሪፍ ነው ቀጥሉበት

February 10, 2011

Anonymous said...

ደጀ ሳላማውያን የእግዚአብሄር ሰላም ይብዛላችሁ።
ብዙ ግዜ የማይመቿችሁን ጽሁፎች ለህዝብ አታቀርቡም ወገኝተኛ ናችሁ ይባላል። ዛሬ እኔም ይህችን ጽሁፍ ልኬ ልታዘባችሁ ነው። ታቀርብዋት ይሆን? አ ምላክ ይርዳኝ

ይህ ስለ ክርስቶስ ተሰጥቶአችኋልና፤ ስለ እርሱ መከራ ደግሞ ልትቀበሉ እንጂ በእርሱ ልታምኑ ብቻ አይደለም፤2 ኛ ቆሮንቶስ 1:29

መቼም በጣም የሚያሳዝን ነገር ነው የምናነበው። በየዘመኑ የጌታ ሃዋርያት መከራቸው አያበቃም። አምላክ ግን ሁሉን ያሳልፋል። ይሄም ቀን ያልፋል ያለፉት ግዜአቶች እንዳለፉት። መምህር አሰግድን እንዴት እንደተረካችሁት ሳነበው በቤተክርስቲያናችን ውስጥ የሚሰሩ ድራማዎች ምን ያህል እንዳደጉ ያሳያል። እውነት ግን ከዚህ ይለያል። እውነት ሁልግዜ ነጻ ያወጣል። ወሬም ወሬ ሆኖ ያልፋል ከሳሾችም በምድር ወይንም በሰማይ በተራቸው በእውነተኛው አምላክ ፊት ይቆማሉ፤ በጣም የሚያሳዝነው የመምህር አሰግድ ስም መጥፋት ዘመቻ አይደለም ያለድካም ለረጅም ግዜ በጌታ አገልጋዮች ላይ ከሳሽ የሆነው የሰይጣን አገልጋይ የሆኑት ሰዎች ህይወት ነው። መቼ ይሆን ብርሃን የሚበራላቸው፤ ከጭለማ የሚወጡት፤ በሚከሷቸው አገልጋዮች ላይ አድሮ የሚሰራውን መንፈስ ቅዱስ የሚያከብሩት?እውነት ክርስቶስ በደሙ ለመሰረታት ቤተክርስቲያን መቆርቆር እንዲህ ነው? በሰውች ዘንድ ማስተዋል እንዲህ ጠፍቷል? አምላክ ደግ ዘመን ያምጣ!!! መምህር አሰግድ እግዚአብሄር ፊቱን ያብራልህ። በጸጋ ላይ ጸጋ ይጨምርልህ። ስለክርስቶስ ወንጌል እንደወርቅ እየተፈተኑ በመከራ ውስጥ ጸንተው ከቆሙት ኦርቶዶክሳውያን መካከል አንዱ ነህ። ይህን ደግሞ ማንም ለእውነት የቆመ ስለእውነት ይመሰክራል። ጌታ ያበርታህ። ያልተረዱህ አንድ ቀን እንደሚረዱህ እናምናለን። እነቅዱስ ጳውሎስ ስለቃሉ እየታረዱ ቢያልፉም በትጋት ያሳለፉት ዘመን ውጤት ዛሬ ላለነው ክርስቲያኖች ብርታት ሆኖናል። በክርስቶስ ያላመኑትን እያሳመንክ የጌታ ምርኮ ያደረካቸው ክርስቲያኖች በእግዚአብሄር ፊትም በቤተክርስቲያን ፊትም ምስክሮችህ ናቸው። ሁሉም ስለራሱ ያስተውል።
የድንግል ማርያም ምልጃ
የመላእክቱ ጥበቃ ከአንተ ጋር ይሁን።

February 10, 2011



ማህበረ፥ክርስቲያን said...

የደብረ ይባቤ ቅዱስ ያሬድ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ እና የዉሉደ ያሬድ ሰንብት ት/ቤት አመራርም ከመላው አባሎቻችሁ ጋራ፣ አመቺ ጊዜ እየጠበቀ ስውር ተልእኮውን ለማስፈጸም ያልተቋረጠ ሙከራ ያደረገውን የኑፋቄ አቀንቃኝ በጥብዐተ ኅሊና በቀጣይነት በማጋለጥ በፈጸማችሁት አብነታዊ ተጋድሎ ኦርቶዶክሳዊ ግዴታችሁን በመወጣታችሁ ያለንን የላቀ አክብሮት እንገልጽላችኋለን።
ቸሩ አምላክ ሁላችሁንም ይባርካችሁ ይጠብቃችሁ።
ሁላችንም በፆምና በፀሎት ስለ ሃይማኖታችን እንለምን!!!

February 10, 2011



ማህበረ፡ክርስቲያን said...

ደጀ ሰላሞች wossene ያቀረበው አስተያየት ማለት ጀርመን ስለሚገኘው የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ በጣም ቢታሰብበት ጥሩ ነው ብዙ ሰዎች ወደ መናፍቅነት ለውጧል።በጣም የሚገርመው በግልጽ ነው የሚሰራው።ማጣራትም ለሚፈልጉ ስሙ (ቀሲስ?)ገዳሙ ይባላል።

February 10, 2011

Anonymous said...

The third recommender:
1. U said that this is fabrication (lie), if so r u saying dejeselam fabricated it or all the people who said that he is Tehadiso are wrong?
2.If he does not have such problems, why was his diploma suspended and why did the college dismiss him from his degree program? Are you saying the information is wrong or though the cases r correct people misunderstood him?
3. If people proved that he says Jesus is praying for us now and that he does not value the holy communion, how dare u call him orthodox?
4. If he attends protestants' why do u call him orthodox and why do u wish the intercession of the Virgin and Angles for him when he does not need them?
5. From what u have said, I suspect u r a Tehadiso, too.

February 10, 2011

Anonymous said...

Good job dejeselamawian. We should hunt and dissociate this menafikan from our holly Orthodox church.

February 10, 2011

Anonymous said...

do you know WHAT this guy is doing HARAR?
They were totally controllong one church and he said he came from techological college and creating big problem.Ene lemenager yemiyasiteyif sera seretewal::
I know him, and his group. if u are geniune find some evidence::
yezani gize serasikiyaje keneberut abat nibure ede kifile yohanis (now u find him in paulos college) ask.

so we refere several fathers who were in harar and knows the problem of this guy. ahunim wede tiwoloji bayihedi zem neber yemibalewu
gowadegnochus harar yibetebitu yeneberu::
Dejeselam if possible harar medhanialem yeteserawun lemawutat mokiru

mulatu ke harar

February 10, 2011

Anonymous said...

ደጀ ሰላሞች እንደምን ከርማችኋል?

መቼም እንደምታውቁት ክርስቲያን ተስፋ
አይቆርጥምና ከዚህ በፊት በጣም ጠቃሚ
ናቸው ብየ በብሎጋችሁ እንድታወጡት ድጋግሜ
ፅፌ ነበር። ነገር ግን አንዱንም አላወጣችሁትም።

የሆነው ሆኖ እኮ አንዳንድ ቀንም እኮ በዋልድባም
ይዘፈናል ይባል የል እንዴ እስቲ እንደ 3 ተኛው
ግሩም ድንቅ እውነተኛ አስተያየት እንደሰው ክርስቲያን
ብታውጡልኝ ብየ እንደገና ተስፋ ሳልቆርጥ ይህችን
አስተያየት ለመሞነጫጨር ተነሳሁ። አምላካችን ጌታችን
መድሐኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልቦናችሁን ያብራላችሁና፣--

ቀደም ሲል ኢትዮጵያ ደርግ በነበረበት ጊዜ በጎጃም
ክፍለ ሀገር ባልሳሳት በእናርጅ እናውጋ ወረዳ አስተዳዳሪ
ነበር። ስሙም ቆምጬ አምባው ይባላል። በመሠረተ
ትምህርት ዘመቻ ላይ የአገሩ ሰው እንዲማር ወይም
እንዲሳተፍ ቢያስነግር ቢያስነግር ገበሬው ወደ እርሻውና
ወደ እለት ተግባሩ በቻ ያተኩራል። በዚህ ጊዜ ጓድ ቆምጬ
አንድ አዋጅ አስነገረ። ይኸውም መሠረተ ትምህርት የማይማር
ወይም የማይወጣ - ቡዳ - ነው። ብሎ ያሳውጃል። በዚህ ጊዜ
የአገሩ ህዝብ - ቡዳ - እንዳይባል በመፍራት እየወጣ ይሄድ
ጀመር።
ይህን ምሳሌ ያስታውስኩበት ምክንያት፡- ቤተክርስቲያናችን

መኖሪያችን፣ ቀያችን፣ ክፉና በጎውን ለይተን የተማርንባት፣
የዘላለም ህይወት ለማግኘት የምንፀልይባት፣ መፅናኛችን፣
ፍቅራችን፣ ትዳራችን ናት ብሎ በእውነተኛው መንገድ ነቃ
ብሎ የሚኖር ፣ የሚታይ የተዋህዶ ክርስቲያንን ከቤቱ ፈንቅሎ
ለማውጣት ሰይጣን የማይሸርበው ድር የለም። ነገር ግን በጣም
ደስ የሚለው ነገር ዳኛችንና አምላካችን እግዚአብሔር ፣
ጠበቃችን የጌታ እናት ድንግል ማርያም፣ ጠባቂዎቻችን
ቅዱሳን መላዕክት ስለሆኑ በጠላት ድንፋታ በፍፁም አንፈራም።

ምንም እንኳን የቀደመው ጠላታችን መልኩን ቀይሮ በስም ማጥፋት
አዋጅ ቢያስነግርም፡ ከቤታችን አንወጣም። ቡዳ ላለመባልም
ብለን አናስመስልም። እንኳን ለድንቢጥ ፡ ለዝሆንም አንደነግጥ።
እውነትና ንጋት እያደር ይገለጣልና።

አንተ የመንፈስ ቅዱስ ወንድሜ መምህር አሰግድ ሳህለ ግን
እግዚአብሔር በሀይሉ በጥበቡ አፅንቶ ያቁምህ። እስከ መጨረሻው
ድረስ የፀና እርሱ ይድናል ነውና ጠላት የፈለገውን ቢያወራ
ቢያስወራ በፍፁም አትፍራ። ስጋና ደም የሚገሉትን
አትፍሩ።፤ ይልቁንስ ነፍስን ወደ ገሃነብ የሚጥለውን እንጂ።

በሉ ደጀ ሰላሞች ሰላም ሁኑ።

February 11, 2011

Anonymous said...

ባለፈው ሳምንት(ጥር 21) ኮተቤ(መሳለምያ) ማርያም ቤቴክርስትያን ሲያስተምር ነበር ኮ

February 11, 2011

full said...

yenanten mecheresha yasayegn .haylachew bezu sehon telatinetachehu banasu lay beza mahibere setanoch.enanten belo deje selam yesw enbana demi yetemachew

February 11, 2011

ssbb23 said...

የሚገርመው አሰግድ ከፕሮተንስታንቶች ጋር እየዋለ ያዉም ከአንድ ሰንበት ት/ቤት አስተማሪ የማይጠበቅ ስራ እየሰራ
በግልፅ እየሱስ አማላጅ ነዉ እያሌ ኦርቶዶስ ነኝ እንዴት ይላል?
ለማንኛዉ እሰስ ገሰስ አባሎቹን በመንጠቆ እየሳቡ ማዉጣት እና የእናት ጡት ነካሾቹን ፣ ነገም ሃገርን የሚሸጡ
አባቶቻቹን ዋሻ ዉስጥ ተጠልለዉ ብራና ልፊዉ ቀለም በትብጠዉ ያቆዩልን ሃይማኖትን ማሳደድ ምን ይሉታል አስግድ
ይቺ ሃይማኖት ብዙ ፈተና እስካሁን ደርሶባታል ግን ሁሉንም በእግዚአብሔር ረዳትነት አሸንፋለች
በጀጂ ክፍለዘመን በካቶሊኮች ቡሁአላም በክባቶች አሁን ደግሞ በ ሉተራዉያን እየተፈተነች ነዉ ።

ነገሩ ክርስትና ያለፈተና አይጥምም ፣ፈተናዉ ይቀጥላል ኦርቶዶስ ታሸንፋለሽ ማን ለዚች ቤተ ክርስቲያን እንደምያስብ ቢዘገይም አየለየ ነዉ።
sb

February 11, 2011

Anonymous said...

Why you are driving him to enter into protestantism if he is not voluntary?

You will be Shamed before God.

February 11, 2011

Anonymous said...

የእግዚአብሔር አብ በረከት፣
የእግዚአብሔር ወልዱ ቸርነት፣
የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዳስ አንዱነት፣
የእመቤታችን የቀዲስት ዱንግል ማርያም አማላጳነት፣
የቅዲሳን መላእክት ተራዳኢነት፣
የጻዱቃን የሰማዓታት ፀሎት፤
የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖታችንን ይጠብቅልን አሜን።
ይህን ሁለም ሰው ሊያውቀው የሚገባ ትልቅ ምስጢር ነው እኔም የተቻለኝን ሁሉ ለማስተላለፍ እጥራለሁ። እናንተም በርቱ።

February 11, 2011

Anonymous said...

Great Job DJ. Many thanks for the info you posted.Every true orthodox christians should know all about this issue. The church of God will always win at the end!!!!

February 11, 2011

Anonymous said...

ውድ ደጀሰላሞች
በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ አሜን ያቀረባችሁት የፕሮቴስታንት ተሃድሶ አቀንቃኝ ላለፉት ጊዜያት የተከተላቸው መንገዶች ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከዚህ በኋላ ልትከተልና በየዋህነት የሰበሰበቻቸውን ልትመረምር እንደሚገባት፣ እኛም ልጆችዋ እግዚአብሄር ቤቱን እንዲያድስ እንዲሁም በጸሎቱ ግዳጅ የሚፈጽም ደግ የሀይማኖት አባት እንዲሰጠን ፤ያሉትንም በጽናት እንዲጠብቅልን ሁሌም አምላካችንን በመለመን መንፈሳዊ አስተዋጽዖ ማድረግ፣ ይጠበቅብናል። በዚህ አጋጣሚ የደብረ ይባቤ ቅዱስ ያሬድ ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ት/ቤት ለረጅም አመታት ይህን ሰውና ማንነቱን በመግለጽ ብዙዎች እንዲጠነቀቁ በማድረጋቸው እናመሰግናቸዋለን።

መናፍቃን ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ሰርገው ለመግባትና ለማጥፋት ወደኋላ አይሉምና እግዚአብሄር ይርዳን። ሌላው በያንዳንዱ ካህን ላይ ያለውን የኑሮ ጫና በመቀነስ በድህነታቸው እንዲሁም በሌላ ደካማ ጎናቸው ምክንያት የደረሰውንና እየደረሰ ያለውን ጥፋት ለመቀነስ ብሎም ለማስወገድ የቤተክህነት አባቶችን እንዲሁም የምዕመኑን ጥረት ይጠይቃል።በተደጋጋሚ እንደምንሰማው ሁሉም መንፈሳዊ ኮሌጆቻችን በፈተና ውስጥ ናቸው፣ ጠላትን መከላከል የሚቻለው ማንነቱ ሲታወቅ ነው፣ በመሆኑም በየጊዜው የምታደርሱን መረጃዎች ህዝቡም ሆነ አባቶች እንዴት ማሰብ እንዳለብን መንገድ ከፋች ነው ። ብዙዎቹ በየቤተ ክርስቲያኑ ያሉ አባቶች ልክ እንዳሁኑ እንድትጠነክሩልን እመብርሃን ትርዳችሁ ትርዳን። የጻድቃን የቅዱሳን አምላክ ቸርነት፣ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን፣ አሜን።

[February 11, 2011](#)

hareg said...

መ/ታ ጉ /ካ
ደጀ ሰላሞች ለኦርቶክዶሳውያን አጥንትን የሚያለመልም ለመናፍቃን አንገት የሚሰብር ዜና ስላስነበባችሁን ቃለ ሕይወትን ያሰማችሁ። ነገር ግን ይህ አሰግድ የተባለው መናፍቅ ብዙ ጀሌዎች እንዳሉት እገምታለሁና በቤተ ክርስትያን ውስጥ አሁንም ተመሳስለው ያሉ ጀሌዎቹን ለማጋለጥ ታላቅ ጥረት ይጠይቃልና ሁላችንም ክርስቲያናዊ ግዴታችንን መወጣት ይጠበቅብናል። በጣም የሚገርመው ደግሞ ከዚህ በላይ አስተያየትየሰጡ አንዳንድ መናፍቃን የቅድስት ድንግል እመቤታችንን እና የቅዱሳንን ስም መግብያ አድርገው በመጀመር የተለመደው ኑፋቄያቸውን የሚዘሩት አንታወቅም ብለው ከሆነ በጣም ተሳስተዋል። ከፍሬያቸው ፈፅመው ስለሚለዩ ባይዘባርቁ መልካም ነው። ለነሱ ''አፍንጫ ሲመታ አይን ያለቅሳል ሲሆንባቸው'' እኛ ደግሞ ''እኛም አውቀናል ጉድጋድ ምሰናል'' ብለናልና።

[February 11, 2011](#)

tewahedo said...

Thanks for the information.

Asegid is either doing his mission or he is confused.

Are these guys trying to deceive themselves or really the want to take people? If they don't believe the Orthodox Dogma why they don't leave the church and follow their own religion? If they believe the church's teachings why the make such trouble? "YEBEG LEMID"

If people are really following the teachings of the church, they will not leave the church though they are named Tehadiso. If they are here just for their own purpose they will leave the church once the church ignores them.

[February 11, 2011](#)

Anonymous said...

Some tehadiso people blame mahibere kidusan to be the reason why they joined protestant church. Please do they think they are talking to a baby? Nobody would go to other religion which has a very different view of God if they don't bleive in it. Mahibere kidusan is trying to clean the church of these kinds. If you are a real orthodox tewahido, nobody would bother you, but only when you have something behind. Mahibere Kidusan Egziabher Yibarkachihu. Deje Selam Emebet tirdachihu.

February 11, 2011

Anonymous said...

ይህን ስሰማ በጣም ነው ደስ ያለኝ አሰግድ ማለት የለየለት ፕሮቴስታንት የሆነው ዛሬ አይደለም ግን ቢዘገይም መባረሩ በጣም ጥሩ ነው
ቤተክርስቲያናችን ይህን የማጥራት ስራ እድትቀጥል እደራ እላለሁ

February 11, 2011

Anonymous said...

ቸር ያሰማን

February 12, 2011

Anonymous said...

Hi it was very courageous and appreciable what you are going to do is. Please be conscious there are also other actors who have the same Mission as Asigid. Thank you!!!!!!!!!!!!1

February 12, 2011

Anonymous said...

እንደምን ከረማችሁ!
አንዳንድ ሰዎች የኑፋቄ ትምህርት እዚህ ላይ ሲውገዝ የ ወንጌል ተቆርቋሪዎች ይመስላሉ። ወንጌል ና ኑፋቄ ይለያያሉ፤ ወንጌል እውነት ስትሆን ኑፋቄ ግን ሃሰት። ያለበለዚያ እነሱስ እነማን ናችው? "አንዳንዶች በስሜ ይመጣሉ..."የተባለውን አንዘንጋ!
ቸር ያሰማን

February 12, 2011

Anonymous said...

"Eyadere-Addis" yilutal yehe new!

February 12, 2011

Anonymous said...

ወገኖቼ
አስተያየቶቹን ሳነብ የገረመኝ ነገር አለ። ለካስ ከተከላዎቹ አንድ አንዱን የምናውቅም አለን። ግን ምን አደረግን ? ቤተክርስቲያን ማለት እኛ አይደለንም ? እኛዉ ካልጠበቅናት ማን እንዲጠብቅልን እንፈልጋለን ? እያወቅን ዝም የምንል ካለን ተከላውን እያገዝነው ከተከላው ጋር እየተባበርን መሆኑን እናስተውል። የምናውቀው ነገር ካለ ለቤተክርስቲያኑ አስተዳደር ካልሆነም ለሀገረ ስብከቱ ወይንም በ Blogs ላይም ማሳሰብ ማስታወቅ ሌላውን ማስጠንቀቅ ይገባናል ግዴታችንም ነው። ወገኖቼ በጊዜ ካልጮህን የሚረዳም አይደርስልንም እራሳችን ስንጠፋ ዝም ብለን እያየን ነው ማለት ነው።

የዛሬ አንድ አመት ከስድስት ወር አካባቢ አስታውሳለሁ አንዷት ወጣት እህት ቁጥራቸው ከመቶ በላይ ምእመናን በተሰበሰቡበት ጉባኤ መካከል ስለ አንድ መምህር የምታውቀውን ከቤተክርስቲያን አስተምሮ የወጡ መሆኑን አስታወቀች። ከጥቂቶች በስተቀር ሰው ሁሉ እርሷን ተናገሯት ነቀፏት ተጮኸባትም። ይህ እንደሚሆን ከማስታወቋዋ በፊት አታው አይመስለኝም ነገር ግን ቤተክርስቲያን ስትጎዳ ምእመኑ ሲመረዝ ዝም ብዬ አላይም በማለት ተነሳስታ እንጂ። የብዙዎች አለማወቅ ይህችን እህት ስህተተኛ አስባላት። ነገር ግን እውነት በህዝብ ብዛት አይወሰንምና ጊዜው ደርሶ መምህሩ ከቤተክርስቲያን ታገዱ። ምንም ተቃውሞ እንደሚመጣባትም አስቀድማ ብታውቅም ይህች እህት የተቻላትን በማድረግ ቢያንስ በጊዜው ሌሎች እንዲነቁ እንዲጠነቀቁ እንዲያስተውሉ አድርጋለች።

ዋናው መልክቱ ወገኖቼ ለቤተክርስያናችን የተቻለንን እናድርግ እንጠብቃት ነው። Information እየሰበሰብን እውነቱንም እያወቅን ግን ጥፋት ስህት እያየን ዝም አንበል። ይህች እህት ምሳሌ ትሁነን። Information የሚሰጡንን በርቱ ማለት መልካምም ቢሆን ይህ ብቻ በቂ አይደለም። የደጀ ሰላምም ዋናው አላማ ደክመው ጊዜአቸውን ገንዘባቸውን ሰውተው የሰጡንን Information እንድንጠቀምበት እንድንሰራበት ይመስለኛል። ከላይ እንዳነበብነው አንድ ግለሰብ 20 አመት ሙሉ እስካሁን ድረስ ባለማቋዋረጥ እየደከመ ያለው ቤተክርስያናችን ላይ ጥፋትን ለማድረስ ነው። ሰይጣን መቼስ ለጥፋት ደክሞ ያውቃል? እንደዚህ አይነቶችስ ሌላ ስንት ይኖሩ ይሆን?

ወገኖቼ እኛ ዝም ካልን ሰይጣን ስህተትን ጥፋትን ሀጥያትን ነው የሚያስለምደን። እኛ ደግሞ የለመድነውን ለልጆቻን ካስተላለፍን እነርሱ ያለነዚህ የሚያውቁት ነገር አይኖርም። ለኛ ብቻ ሳይሆን የሚቀጥሉትንም ትውልዶች ለማትረፍ በቤተክርስቲያን ውስጥ ስህተትን ጥፋትን እያየን ዝም ማለት የለብንም። መጠየቅ መናገር ማስታወቅ ማመልከት ማሳሰብ መቃወም የሁላችን ግዴታ ነው። ከያሬዳዊ ዜማ የተለየ ነገር መጀመሪያ ሲጀመር ወላጆቻችን ቢቃወሙ ቢጮሁ ኖሮ ዛሬ ከያሬዳዊ መዝሙራት ሌላ ባላወቅን ነበር። ዘሬ ያሬዳዊውን ለይቶስ የሚያውቅ ስንቱ ነው? ስዚህ ወገኖቼ ዘም ብለን ተቀምጠን ተኩላው ከነከሰን በሗላ ሳይሆን ገና ከሩቁ ስናየው ነው መናገር ማስታወቅ መጮህ ያለብን እራሳችንንም ወንድም እህቶቻችንንም ልጆቻችንንም ቤተክርስቲያናችንንም ለመጠበቅ።

እግዚአብሔር አምላክ ይርዳን

February 12, 2011

Anonymous said...

tade from dilla
Asseged is already known and isolated but i worry about his friend who hide themselves in the church and do the same activities.
He was invited by mr.Begashaw and Yared Aademe to preach in big conference in dilla so many times.so the responsible body will take a

- ► January (17)

- ► 2008 (151)
  - ► December (35)
  - ► November (10)
  - ► October (11)
  - ► September (4)
  - ► August (2)
  - ► July (4)
  - ► June (4)
  - ► May (10)
  - ► April (23)
  - ► March (18)
  - ► February (9)
  - ► January (21)

- ► 2007 (67)
  - ► December (1)
  - ► November (3)
  - ► October (11)
  - ► September (10)
  - ► August (9)
  - ► July (6)
  - ► June (12)
  - ► May (5)
  - ► February (4)
  - ► January (6)

- ► 2006 (32)
  - ► December (16)
  - ► November (16)

**Deje Selam: Blogging Since November 2006. (dejeselam@gmail.com)**

## D.Selamaweyan/ ደጀ ሰላማውያን

### ደጀ ሰላምን በኢሜይል

ኢሜይሎትን እዚህ በማስገባት ደጀ ሰላም ላይ የሚወጡ ጽሑፎች በሙሉ እንዲላኩሎት ማድረግ ይችላሉ (Enter your email address here):

dejeselam/XLtN en_US Subscribe

By ደጀ ሰላም DejeSelam

## የአቡነ ጳውሎስ "ሐውልተ ስምዕ"

## ጽሑፎችን በቀላሉ ለማግኘት

Add to Google netvibes newsgator MY YAHOO!

Posts

Add to Google netvibes newsgator MY YAHOO!

Comments

## ቅዱስ ሲኖዶስ የብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስን ውግዘት አንስቶ ሥርዓተ ቀብራቸው በኢትዮጵያ እንዲፈጸም፣ አስከሬናቸውም ለጵጵስናቸው በሚገባ ክብር፣ አበው ጳጳሳት በሚያርፉበት በመ/ፀ/ቅ/ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን እንዲያርፍ ወስኗል። በዚሁ በአሜሪካን አገር እንዲቀበሩ የሚፈልጉም አሉ። እርስዎስ በየት እንዲፈጸም ይመርጣሉ?

# Labels

- ሐተታ (324)
- ዜና (118)
- ቃለ ምልልስ (4)
- ኪን (4)
- ርእሰ አንቀጽ (3)
- ማስተዋወቂያ (1)

## Links

- Adebabay
- Bete Dejene
- Deje Berhan
- Deje Selam Mezmur ደጀ ሰላም መዝሙር
- Kesis Yared
- OCA
- Qedamawi

## Popular Posts

- የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ አፅራረ ቤተ ክርስቲያንን ለመከላከል በሚያደረገው ጥረት ማንኛውንም ድጋፍ እንደሚሰጥ የአ/አበባ ሀ/ስብከት አስታወቀ
- የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተዘረጋባትን የተሐድሶ ወጥመድ ይፋ አድርጓል የተባለ “ሰነድ” ይፋ ሆነ

## Join us on Facebook

ደጀ ሰላም Deje Selam




Create Your Badge

## Welcome to Deje Selam

- ደጀ ሰላም
- zetewahedo

## Deje Selamaweyan